# የመለስ አምልኮን በጨረፍታ (ክፍል አራት)

## በሰው አጀንዳ አትንጫጫ!!

**ዮናስ 7/20/12**

በነፃ ፕሬስ ስም ፈቃድ አውጥተው፣ የመፃፍና መረጃ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ከለላ አድርገው በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ገበያ ውስጥ የማስተውላቸው የሃገሬ ጋዜጦች ፈቃዳቸው ነፃ ፕሬስ ስለመሆኑና የሚጠቀሙትም መብት መረጃ የማግኘትና የመፃፍ ስለመሆኑ በእጅጉ የሚያጠራጥረኝ እንደሆነ በመጣጥፎቼ በተደጋጋሚ ጣጥፌያለሁ።

የሊቢያንና የግብጽን አብዮት ተከትሎ የአመጽና የትርምስ ጥሪያቸውን ሲያስተጋቡ ከነበሩት ጋዜጦች ውስጥ ዋነኛ የሆነችው ፍትህና አምደኞቿ ደግሞ ከአረቡ አለም አብዮት በኋላ ባሰባቸው ቢባል እንጂ የሁከት ዜናቸውና መጣጥፋቸውን መለጠፍ ከጀመሩ በርካታ ጊዜያት አልፏቸዋል።

የአረቡ አለም አብዮት በኢትዮጵያ እንዲደገም ያልፈነቀሉት ድንጋይ ባይኖርም ነገሩ መሰረታዊና ተጨባጩን የሃገራችንን ሁኔታ ያላገናዘበ የትርምስ ሃይሎች አጀንዳ በመሆኑ አልተሳካም። በዚህ የተቆጨት ፍትህና አምደኞቿ የነግብጽን አብዮት ተከትሎ የተፈጠሩ አጋጣሚዎችን በተለይም የአወልያውንና የመጅሊሱን፣ የዋልድባ ገዳምና ጉራፈርዳን ለአመጽ መቀስቀሻ በመጠቀም እሪታቸው እስካሁንም ያልተቋረጠ ሲሆን ኡኡታው ግን የገደል ማሚቶ ጩኸት ሆኖ እዛው ነጥሮ ወደራሳቸውና ወደዜሮ ድምር ስብስቡ የሚመለስ ሆኗል።

የመለስ አምልኮን በጨረፍታ  ሶስት ተከታታይ መጣጥፎች በአብዛኛው የተገነዘብነው ይህንኑ ለአመጽ የሚዳርጉ ሙከራዎችንና የከሸፉ ጥሪዎችን ሲሆን የቋመጡት ትርምስ ይሳካ ዘንድ የማይገናኙ ጉዳዮችን በቀጭን ገመድ ማገናኘት፤ የሌሉ ሁነቶችን ያሉ አስመስሎ በማቅረብ፣ ያቃዣቸውንና በህልማቸው ሁሉ ያዩትን ዕውነት አስመስሎ በማቅረብ፣ በቤታቸውና በቤተሰባቸው አካባቢ የተስተዋሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የመላው ኢትዮጵያውያን አድርጎ በማቅረብ ብዙ ብዙ ቢለፍፉም ያልተሳካ እንደሆነ የተመለከትንባቸው አጀንዳዎች ናቸው። የተመስገን ደሳለኝ የመለስ አምልኮ ክፍል አራት የመጣጥፍ ጥርቅምም ከ3ቱም ክፍሎች ብዙ ያልተለየ የዜሮ ድምር አስተሳሰብ በስፋት የሚገለጹበት አጀንዳዎች የተነሳባቸው ናቸው።

በክፍል አራት ላይ ለሚገኙት የመጣጥፍ ጥርቅሞች የተሰጠው ዓቢይ ርዕስ "አንዳንድ ነጥቦች ስለፓርቲዎቻችን" የሚል ቢሆንም በዚህ ዓቢይ ርዕስ ስር በሚገኙት ወደ 6 የሚጠጉ ነጠላ ርዕሶች የሚያጠነጥኑት ያው የተለመደው ስለኢህአዴግ ነው። ለማደናበርና ስለፓርቲዎቻችን የሚለውን ብዙ

ቁጥር ለማምታታት ኢህአዴግን ወደ ብሄራዊ ድርጅቶች ዘርዝሮ ብአዴንን ኦህዴድን፣ ደኢህዴንን እና ህወሀትን የነጠላ ውግዘት ያወረደባቸው ተመስገን ከወቀሳ ለመዳን በሚመስል ወይም በአራድኛ |ጅካ ´ ሊይዝብን እንደአሸን ከፈሉት የተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል የተወሰኑትን መርጦ ላይ ላዩን ሄዶባቸዋል።

የክፍሉን የመጀመሪያ ርዕስ ስንመለከትም የምናስተውለው ይህንኑ ነው።ርዕሱ |ኢህአዴግና ሙስና የአንድ ሳንቲም ግልባጮች ´ ይላል ።ወደዝርዝሩ ስንገባ የምንመለከተው ደግሞ ወደኋላ በርከት ያሉ ዓመታትን ተጉዘን ያየነውንና መልስ የተሰጠበትን የአለም አቀፉን የልማት ፕሮግራም (UNDP) ዓመታዊ ሪፖርት ነው። ይህ ሪፖርት በወቅቱ የአፍሪካ ሃገራትን የወጪ ንግድ በተመለከተ ፤ የምዕራባውያኑን ተጽእኖ ፍትሃዊ የገበያ ስርዓት ያለመኖርና የአፍሪካ አገራትን የተወዳዳሪነት አቅም የዳሰሰ ሲሆን በአናቱም ሃገራት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት አዲስ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በወጪ ንግድ በኩል የሚንቀሳቀሱት ገንዘቦች ለሙስና የተጋለጡ መሆናቸውን የሚያትት ነበር።

ይህን ሪፖርት መሰረት በማድረግ እንደተለመደው |ውስጥ አዋቂ ምንጮች´ በምትለው ካባ እስክንደር ነጋ 8.4 ቢሊዮን ብር ከኢትዮጵያ መዘረፉን በማይጨበጡ ማስረጃዎች ሊተነትን ሞክራል።

ትንታኔውንም ተመስገን፣ የዜሮ ድምሩ ስብስቦች እና የፍትህ አምደኞች በተለያየ መንገድ ከማይገናኙ ነገሮች ጋር በማገናኘት እና በማጋነን ለማስተጋባት ቢሞክሩም ቀድሞ ነገር ትንታኔው ተጨባጭ ያልሆነና (UNDP) ሪፖርት ጋር የሚያያይዘው አንዳች ነገር የሌለው በመሆኑ ሰሚ ሳያገኙ ቀርተዋል። "ኢህአዴግ እና ሙስና የአንድ ሳንቲም ግልባጮች" በሚለው ርዕስ የተወሳው ደግሞ ዓመታት ያለፉት የUNDP ሪፖርት ነው።

ለምን? የሚል ጥያቄ ስናነሳ ነው ጊዜው ያለፈበት አጀንዳ የተነሳበትን ምክንያት የምናውቀው። የዚህ አጀንዳ መነሾ በኔ በኩል ሁለት እንደሆነ ደርሼበታለሁ። አንደኛው እስክንድር ነጋ በሽብር ተጠርጥሮ በታሰረበት ወቅት መፃፉ ሲሆን እስክንድርን ታታሪና የሃገሩ ተቆርቋሪ በማድረግና በማጀገን በተዘዋዋሪ ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ በማስቀደም ህዝቡን እስክንድር |ነፃ´ ነው ወደሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ለማድረስ የተፃፈ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ የUNDPን ሪፖርት ከሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ የከሸፈው አብዮት ዳግሞ ነፍስ ይዘራ እንደሆን ለመሞከር ነው። |ይህ ህዝብ የተዘረፍኩትን ገንዘብ እራሴ አስመልሰዋለሁ ያለ ዕለት ጉድ መፍላቱ አይቀርም የዚህ አይነት ጉዶች ደግሞ ነበልባላቸው ከእሳተ- ገሞራም የበረታ ነው´ ገጽ 179 |የብዴን ሰዓት ስንት ላይ ቆሟል? ´ ይላል ቀጣዩ የተመስገን መጣጥፍ። ጅማሮውም ብአዴን በባህርዳር ከተማ ላይ የገነባውን የሰማዕታት ሀውልት በመሸንቆጥ ነው።

የጎንደር ከተማን ከብአዴንና ከጎንደር ከተማ ልማት ጋር በማያያዝ ውጤቱን 30 አመት ሞላኝ የሚለው ብአዴን ሳይሆን የነገስታቱ የደርግና ከፍ ካለም የኢህዴን ያደርገዋል። ኢህዴን ስያሜውን ወደ ብአዴን የለወጠበትን ምክንያት ሲያብራራም መአህድን ለማጥፋትና ብአዴን የቆመው ለአማራ ህዝብ መሆኑን ለማስመሰል የተሸረበ ሴራ ነው የሚለው ተመስገን ብአዴን ዕድሜዬ ነው ካለም የ18 አመታቱን የኢህዴን ጉዞ መቀነስ አለበት ሲል ይሞግታል።

|ይሄ ማለት ግን ብአዴን እና በችግር የሚማቅቀው የአማራ ህዝብ እጅና ጓንት ናቸው ማለት አይደለም። ምክንያቱም ብአዴን 30ም ሆነ 18 ዓመት ቢሞላው ከስም በቀር በአካል የማያውቃቸው ብዙ የአማራ ከተሞች አሉ።" ገጽ 184

"ወደጎጃም ብታልፉም ያው ነው። ------ ሉማሜ፣ ደንበጫ ፣ አማኑኤል---ወዘተ ወዘተን እግራችሁ እስኪቀጥን ብትዞሩ "የጎጃም ነጭ ጤፍ"ን ተረት ሆኖ ነው የምታገኙት። እነዚህ ሁሉ ከተሞች ዛሬም ከመሰረተ ልማት ጋር ሆድና ጀርባ ናቸው። መድሀኒት ባለውም፣ መድሀኒት በሌለውም በሽታ እንደቅጠል የሚረግፉበት የአማሮችን መንደር ዞራችሁ አትጨርሱትም።የጎጃም ማር የሚርኩሪ ያህል ለምን ተወደደ ብሎ መጠየቅ አይቻልም። አርሶ አደሩ የብአዴን የሆኑ ድርጅቶች በዱቤ የሚሸጡለትን ማዳበሪያ መክፈል የሚያስችል ምርት እንኳ አያገኝም።" ገጽ 184

|አንዳንድ ነጥቦች ስለፓርቲዎቻችን´ የሚለው ተመስገን አሁንም ከብአዴን ጀርባ ላይ አልወረደም። "ችግሩ አካባቢው በሰንሰለታማ ተራራ መያያዝ አይደለም፣ የአማራ ህዝቦች ችግር መንስኤውም እንደህወሀት ወሬ "አማራው በኩራት ታጅሎ ስራ ባለመስራቱ" እንዳይመስላችሁ። ዋነኛው ችግር እያደገ ከመጣው የህዝብ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን የመሬት ፖሊሲ ባለመኖሩ እና የተሻለ የአስተራረስ ዘዴዎችንም ሆነ ለምርት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ማቅረብ ባልቻለው ብአዴን ድክመት ነው።" ገጽ 185

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ)ም የተመስገን ውረፋና ዘለፋ የተንሰራፋበት ተራ ፕሮፓጋንዳ ነው። የብአዴን ሰዓት ስንት ላይ ቆሟል የሚለው መጣጥፍ ተራ ፕሮፓጋንዳ ነው፤ ዘለፋና ውረፋም ነው ያልኩበትን ምክንያት ደግሞ አብራራለሁ፤ በቅድሚያ ግን ህወሃት |የአማራ ህዝብ በኩራት የታጀለና ስራ የማይሰራ ነው።" ´ስለማለቱ በማስረጃ አስደግፎ ቢያቀርበው ኖሮ ጥሩ ነበር። ዳሩ እሱም የሰማው አይመስለኝም ምክንያቱም |የህወሃት ወሬ´ በሚል ነው ያቀረበውና።የሆነ ሆኖ ስለብአዴን ልማታዊነትና ስለአማራ ከተሞች እንዲሁም ስለአርሶ አደሩ ስናወሳ ተመስገን የጠቃቀሳቸው ሁሉ ተራና አሉባልታ ስለመሆናቸው በተጨባጭ መረዳት ይቻለናል።

ከመሰረተ ልማት ጋር በተያያዘ ተመስገን እንዳለው እግራችን እስኪቀጥን መዞር አያስፈልገንም። ከአባይ በረሃ ወይም ከፍልቅልቅ እንነሳና እንጓዝ፤ ከህዳሴው ድልድይ ጀምረን ባህርዳር እስክንገባ በርካታ መጋቢ መንገዶችን ጨምሮ ሸር ብትን የምንልበትን ፤ባህርዳሩ ቀርቶ ጎንደር እለቱን መግባት

የሚያስችለንን መንገድ መካድ መቼም ነውር ነው። ቡሬ-ቤንሻንጉል፤ እንጅባራ ቤንሻንጉል፤ ሞጣ መገንጠያ ዛሬ የሁለት ቀን መንገድ ሳይሆኑ የጠዋት መንገድ ናቸው። ወረታ– ደብደታቦር –ወልድያ በማን ይሆን የተሰራው? አዘዞ -መተማ –ጋላባት፣ ጎንደር –ሁመራ– ማይ ካድሬስ፣ ምነው ተዘነጉ?።

ኩራዝ የሚንጨለጨልባቸው የወረዳ ከተሞች ሳይቀሩ ዛሬ በብርሃን የተሞሉት፤ ከመጅ ጋር የተፋታችውን አርሶ አደርስ ማን ይሆን ከባቡር ቤት ጋር ያጋባት? ብዙ ብዙ ማለት ይቻለናል። የስማዳዋ እናት ነች ወይስ የጋይንቷ ዛሬ ደብረታቦር ሆስፒታል መሄድ ግዷ የሚሆነው?። የአርማጭሆ ህፃናቶች ናቸው ወይስ የጭልጋ ለግላጎች ትምህርት ፍለጋ ስንቅ ይዘው ጎንደር የሚከትሙት? የነመርሃቤቴ ፣የነአንፆኪያ ገምዛ ወይስ የሃርቡ ልጆች ናቸው ትምህርት ጤናና ስራ ፍለጋ ደሴ የሚከትሙት? እግርህ እስኪቀጥን መዞር የለብህም የፈለግኸውን የገጠር ከተማና መንደር ለናሙና ወስደህ በሁሉም አቅጣጫ አንድ ጉዞ ብቻ ማድረግ፤ ጤና ጣቢያዎቹን ፣ጤና ኬላዎቹን፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን ሁሉንም ከነ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞቻቸው እና ቁሳቁሶቻቸው ጋራ ከአማራው ህዝብ ጉያ ውስጥ ታገኛቸዋለህ።

የጎጃም ነጭ ጤፍን ለማግኘት እግራችን እስኪቀጥን የአማራን የገጠር መንደሮች መኳዝ አይጠበቅብንም። ወዳሻን አቅጣጫ ግራና ቀኝ እየቃኘን በዋናው ጎዳና ላይ ብቻ መኳዝ ይበቃናል። የልማት ሰራተኛውና አርሶ አደሩ ከማሳ ላይ ሆነው ወይ በጉልጓሎ ወይ በአረም አልያም በመስኖ ጠለፋ ላይ ወይም ምርት በመሰብሰብ ሂደት ላይ ሳሉ መመልከት ይቻለናል።

ከግብዓት አቅርቦት፣ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር ለተነሳው የተመስገን ሙግት  አንድ ልምዴን ብቻ ባወሳ በቂ ይመስለኛል። ከደብረብርሃን ወደ እነዋሪ ደነባ ሞረትና ጅሩ ነው ጉዞዬ ፤ ለወትሮው ጠፍ መሬት በነበረውና በሄክታር ከ8 ኩንታል በላይ ማምረት በማይቻለው በዚህ መሬት ላይ ጤፍን በችግኝ መልክ አዘጋጅቶ በመስመር በመዝራት እና በ ቢቢኤም (አዲስ ቴክኖሎጂ) ዘዴ ከ35 ኩንታል በላይ በሄክታር ተሰብስቦ አይቻለሁ። ዲገሉ የተባለ የስንዴ አዲስ ዝርያና አረርቲ የሽንብራ ዘርም ውጤታማ ሆኖ በመጠን ብቻ ሳይሆን በጥራትም በፍሬ ክብደትም በፊት ከነበረው 4 እጅ በላይ እጥፍ ሆኖበማሳ ላይ ሳለም ሆነ ሲሰበሰብ  አይቻለሁ። ይህ ደግሞ በሞረትና ጅሩ ወይም እነዋሪ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በመላው የአማራ ክልል በሚገኙ አርሶ አደሮች ኋሮ ተግባራዊ የሆነ ዘዴና በብአዴን /ኢህአዴግ የተገኘ ውጤት ነው።

ወደአልማ ስንመጣ መጀመሪያ ለተመስገንና በተመስገን መጣጥፍ ብዥታ ለገባችሁ የተመስገን አንባብያን www.Amharada.Org.et ከፍታችሁ አልማንና ውጤቱን በመመልከት የተመስገንን በሰው አጀንዳ የመገጫጨት ምክንያት ማረጋገጥ እንደምትችሉ ላስታውስ እወዳለሁ። በመቀጠል የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ)ን የ20 ዓመታት ጉዞ (ከ1984-2004) እና ልማታዊ መንገድ መቃኘት ከባድ ስለሚሆን የተመስገንንና ስብስቡን ሴራ ለማጋለጥ የሚያስችሉትንና ዋና ዋና የሚባሉትን ብቻ በማንሳት የብአዴን ሰዓት ስንት ላይ እንደቆመ? ለጠየቁት ሁሉ ምላሹን እሰጣለሁ።

ሃያን በቅጡ ባልሞላ የወጣትነት እድሜ አንፀባራቂና ለድህነት ጀርባ የሰጡ ህዝባዊ ተግባራትን መከወን የህልም ያህል አጠራጣሪ ነው። አማራ አቀፍ ልማት ማህበር ግን ፈጽሞታል! የሚዳሰስ የሚጨበጥና ሰብአዊ ሃብት የሚያድግበት፣ የጤና ዋስትና የሚያገኝበት ኢኮኖሚያዊ እድገትን የሚያሳልጥበት የማህባራዊ ተቋማት ግንባታዎችን እውን አድርጓል። እጅግ ፈታኝ በሆኑ የክልሉ አካባቢዎች በመድረስ እስከ 38 ሜትር ርዝመት ያላቸው በርካታ ድልድዮችን ጨምሮ ከ160 ኪሎ ሜትር በላይ አዲስ መንገድ በመስራትና በመጠገን የተራራቁ የህብረተሰብ ክፍሎችን አገናኝቷል።

በምእራብ ጎጃም ዞን ጢስ አባይ ከተማ ለጢስ አባይ ወንዝ የድልድይ ግንባታና 1.45 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው መንገድ በ1986 ዓ.ም ተሰርቶ መመረቁ ለምን ይዘነጋል?። በምስራቅ ጎጃም ዞን ቢቡኝ ወረዳ አስቸጋሪውን የጮቄ ተራራ አቋርጦ የሚያልፈውን ሮብ ገበያ ድጎጽዮን የ53 ኪ.ሜ መንገድ ግንባታ በRR30 ደረጃ ከ1987-1989 ባለው ጊዜ ውስጥ አልማ ሰርቶ ማጠናቀቁስ?።

በሳንጃ ወንዝ ላይ የሚያልፈውና ከ58 ሜትር በላይ ርዝመት ያለው ድልድይና 42 ኪ.ሜ መንገድ፣ በዋግ ህምራ ዞን ከድልቢያ ቅዳሚት የሚዘልቀው የ18.5 ኪ.ሜ መንገድ፣ በሰሜን ወሎ ዞን በዳውንት ወረዳ የተሰራው የኮን የነጃ ወይም የእንቊቄ ወንዝ 32ሜ ርዝመት ድልድይ፣ በዋግ ኽምራ ዞን ጽጽቃ ተላጀ 7.5 ኪሎ ሜትር መንገድ፣ በደቡብ ጎንደር ዞን በሃሙሲትና ወረታ መካከል ወደ ዋንዛዬ የሚወስደው መንገድ፣ ሰሜን ጎንደር ዞን ከደባርቅ ሳንቃ በር/ሰሜን ፓርክ 16 ኪሎ ሜትር መንገድ ወዘተርፈ ለአይን ይታክቱ የነበሩ ተራሮች እጅ ሰጥተው መንገድ የሆኑት ከተራራው ጀርባ በሚገኘው አልማ ነው። አማራ አቀፍ ልማት ማህበር ባሳለፈው 20 ዓመት ዕድሜ ከ145 በላይ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ገንብቷል።

በሰሜን ጎንደር ዞን አሁን በግንባታ ላይ ያሉትን ሁለት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን ግንባታ ሳይጨምር 21 የትምህርት ተቋማት ተገንብተው ለአገልግሎት በቅተዋል።

በደቡብ ጎንደር ዞን የተለያዩ ወረዳዎች አንድ ቤተመፃህፍትን ጨምሮ 7 የአንደኛና የሁለተኛ ሳይክል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው ከትምህርት ገበታ ርቀው ለነበሩ በርካታ ህፃናት የዕውቀት ገበያ የሆኑት በአልማ ብርታትና ቁርጠኝነት ነው።የማክሰኚትን ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት የሰከላን ቴክኒክና ሙያ ት/ቤት የሸንዲን መሰናዶ ት/ቤት ሂደህ ማየትና መፃፍ ያባት ነበር ።

የልማት መሪው አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) ጤና ኬላዎችን፣ ታዳጊ ጤና ጣቢያዎችንና ሙሉ ጤና ጣቢያዎችን ጨምሮ 84 የጤና ተቋማትን ገንብቶ ለአገልግሎት አብቅቷል። ደንቢያ ሰሜን ጎንደር ወደመላጀህ መንደር ሂድ የሮቢትን ጤና ጣቢያ ብቻ አይተህ ለአልማ እጅ መስጠትህ

አይቀርም። ካሻህም የእስቴን ጤና ጣቢያ መጨመር ትችላለህ፡፡ 66 የውሃ ተቋማትን በመገንባት ህብረተሰቡ ከውሃ ወለድ በሽታ እንዲጠበቅና የንጹህ ውሃ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረገው ማን ይመስልሃል?። ያ ያፌዝክበትና  የተዘባበትክበት አልማ ነው።

በክልሉ እጅግ ኋላቀር በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ሴቶችን የስራ ጫና ለመቀነስ ከብአዴን በተገኘው ብር 2, 396, 075 በጀት ለተጠቃሚዎች አስፈላጊውን ስልጠና በመስጠት 31 ወፍጮዎችን በመግዛት እቦታው ድረስ በመውሰድና በማስተካከል ተጠቃሚዎች አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረገው አልማ ነው። በአጠቃላይ አልማ በየአመቱ የሚፈፅማቸው ፕሮጀክቶች በአይነትም ሆነ በመጠን እየጨመሩ መጥተዋል። ለአብነት ያህል በ2003 ዓ.ም ጠቅላላ የትምህርትና የጤና ተቋማት ማስፋፊያ በጀቱ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ጨምሮ 20,000,000 (ሃያ ሚሊዮን) የነበረ ሲሆን በ2004 ዓ.ም ደግሞ 45,000,000 (አርባ አምስት ሚሊዮን) ብር ደርሷል። ልብ በሉልኝ ይህ እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ የቀረበ የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) ገድል ነው።

እነ መራራ ጉዲና በየነ ጴጥሮስን፣ቡልቻ ደመቅሳንና ሌሎቹንም የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን ስናስታውስ ቀደሞ ድቅን የሚልብን በየጋዜጣው ላይ የሚሰጡት መግለጫ ነው። ከመግለጫዎቻቸው ሁሉ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው ደግሞ አማራጭ ፕሮግራሞችና የጋራ ሃገራዊ አጀንዳዎች ሳይሆኑ፣ ገዥው ፓርቲ ላይ የሚቀርቡ ወቀሳዎች ናቸው። ከወቀሳዎቹ መካከልም ምህዳር ጠበበብን፣ ምርጫ ቦርድ አደርባይ ነው፣ ያኛው ፖለቲካ ፓርቲ የኢህአዴግ ተለጣፊ ነው፣ ኢህአዴግ አምባገነንና  በአንድ ሰው ቁጥጥር ስር የሚገኝ ግንባር ነው ፤የሚሉና የመሳሰሉቱ ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉ።

ሆኖም እነዚህ አመራሮች ራሳቸው አምባገነንና ለ20 ዓመታት ከያዙት ወንበር አልላቀቅ ያሉ፣ ለውስጠ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የማይገዙና ባሻቸው መንገድ |ህዝቤ´ በሚል ፊውዳላዊ መርህ የሚጓዙ ህዝብን ሽፋን ያደረጉ ግለኝነት የተፀናወታቸውና ያለ እስትራቴጂ በጭፍን የሚጓዙ፤ ከትርምስ ለማትረፍ የሚሹ ሃይሎች ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ ቢነገራቸውም አይሰማም ያሉ ናቸው።

|የተቃዋሚዎች ሰፈር እንደምን ከረመ ?"በሚለው የተመስገን መጣጥፍ ገጽ 188ን ይመለከቷል። |ምክንያቱም በጣም የጠበበ በጭላንጭል ደረጃ የሚያንቀሳቅስ ምህዳር አለብዬ ስለማስብ ነው። የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችም ቢሆኑ በዚህ ይስማማሉ።´ ገጽ 193፤ ተመስገን ይል ይልና ሲደነግጥ ይሁን መሳሳቱን ሲረዳ ብዙ ጊዜ አንድ ነገር ይላል። |በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ይወነጅሉኛል፣ የፍረጃ መጣጥፋቸውን ይለጥፉብኛል" አይነት ነገር።

|ደግሞም እኮ እኔን በደፈናው የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ነው ማለት ሌላ አላማ ከሌለው በስተቀር ስህተት ይመስለኛል። እዚህ ሃገር ብዙ ወሮ በላ´ እና |ጨዋ´ ፓርቲዎች አሉ። ታዲያ የየትኛው ፓርቲ

አባል ነኝ ይኼ መብራራት አለበት።ለእኔም ቢሆን የፓርቲዬን ስም ብትነግሩኝ ለጽድቅ ይሆናችኋል። አሊያ ግን ከመሬት ተነስቶ መለጠፍ ተገቢም፣ ገንቢም አይደለም።´ገጽ193-194

ተመስገን አንተ ከመሬት ተነስተህ ያለጠፍክበትን አንድ መጣጥፍ እንኳ እስቲ አስታውሰን። ነው ወይስ አንተ የመለጠፍ ብቸኛ ባለመብት ነህ። አንተ ስትለጥፍ ተገቢና ገንቢ የሚሆነው በየትኛው አመክንዮ ይሆን?

|የሆነ ሆኖ´ ጣት ከመጠቆሙ በፊት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ራሳቸው የራሳቸውን ጥንካሬ መፈተሽ አለባቸው። አመራሮቻቸውን መገምገም አለባቸው። በምርጫ 2002 ለደረሰባቸው ሽንፈት ከገዢው ፓርቲ ተጽእኖ እንቅፋት በተጨማሪ የራሳቸውንም ድክመት መረዳት የሚኖርባቸው ይመስለኛል። ምነው? |ምርጫው ቀናት ሲቀሩት የአንድነት ፓርቲ አባላት እርስ በእርስ መቧቀሳቸውን አይተንም የለ እንዴ? ።ገጽ 194፤ ከላይ እዚህ አገር |ወሮበላና ´ |ጨዋ´ ፓርቲ አለ ባልከው መሰረት እርስ በርሱ የሚቧቀሰው ከየትኛው ወገን ሊመደብ እንደሚችል ድረስበት፤ በምላሹም የማን አባል እንደሆንክ ማወቃችንን ትረዳለህ።

|ኦህዴድን በጨረፍታ´ የሚለው ቀጣዩ መጣጥፍም ቢሆን የተመስገንን ለጣፊነት እና ትምክህት የሚያረጋግጥና የበፊት ስርዓቶች ናፋቂ መሆኑን በሚያሳዩ እና በሚያመለክቱ ሃሳቦች የታጨቀ ነው። ለማናቸውም |የተቃዋሚዎች ሰፈር እንደምን ከረመ´ የሚለውና "ኦህዴድን በጨረፍታ" የሚሉት የተመስገን መጣጥፎች በተደጋጋሚ ስናገራቸው እና ስገምታቸው የነበሩ ነገሮች ላይ እርግጠኛ እንድንሆን አስችለውኛል። ይኸውም ከተመስገን መጣጥፎች ጀርባ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ እና አቶ አሰገደ ወልደስላሴ ስለመኖራቸው።

ወደ ክፍል አራት የመጨረሻ አጀንዳ ስንመጣ |ኢህአዴግ |አውራ ፓርቲ" ሲል? የሚለውን መጣጥፍ እናገኛለን። በተቃዋሚዎች ሰፈር እንደምን ከረመ መጣጥፉ ተቃዋሚዎችን ንቃተ ህሊና፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የንድፈ ሃሳብ ትንታኔ እና ድርጅታዊ ስትራቴጂዎች ያስፈልጋቸዋል ሲል እና ሲወተውት ይህን ሃሳብ ከፈለገ ደግሞ እንደሚያፈርሰው ቀደም ብዬ በነገርኳችሁ መሰረት  ኢህአዴግ ጋር ሲመጣ፣ የኢህአዴግን የንድፈ ሀሳብ ትንታኔ አደረጃጀትና ስትራቴጂዎች ድርጅታዊ እስትንፋሱን ሁሉ አብንኖ ለማትነን ይሞክራል።

እዚህች ጋር ግን ተመስገን |ጋዜጠኛ´ ነኝ ስለሚለን እንደጋዜጠኛ በመገመት ነው የተቸሁት እንጂ ፖለቲከኛና የተቃዋሚ ፓርቲ አባል መሆኑን ከግምት በመክተት ካሰብነው ግን ለተቃዋሚዎች የመከረውን ኢህአዴግ ጋር ሲመጣ መኮነኑ ትክክል ስለመሆኑ  ይገባናል። በአንድ ወቅት ለንባብ ከበቃችው የኢህአዴግ የንድፈ ሀሳብ መጽሄት  |አዲስ ራዕይ´ ርዕሰ አንቀጽ ተከታዩን በመምዘዝ አቧራ ለማስነሳት እና ነገር ለመጫር ይሞክራል።

|መጽሄቱ´ የተቀመጠለትን ዓላማ አሳክቷል ሊባል የሚቻለው በየወሩ መታተሙና የህትመት ኮፒም ማደጉ ሳይሆን አባላት በየጊዜው ሲያነቡት፣ ሲወያዩበት እና መልእክቶቹን በሚገባ ሲጨብጧቸው፣ ያገኙትንም ግንዛቤ የተግባር መመሪያ አድርገው ሲጠቀሙበት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም´ ገጽ 207፤ ከዚህች የመጽሄቷ መልዕክት ውስጥ ተመስገንን የገረመውና የኢህአዴግን የአውራ ፓርቲነት ግስጋሴ የሚያረጋግጥ ነው ሲል የወሰደው ። "አባላት ከመጽሄቷ የሚያገኙትን ግንዛቤ የተግባር መመሪያ ማድረግ አለባቸው።" የምትለዋ መልዕክት ነች።

ለነገሩ ተመስገን ፍትህና የፍትህን መዋቅር የሚለካው በኮፒ ብዛቷ መሆኑን በተደጋጋሚ በነገረን መሰረት ላይገባው እንደሚችል እንገምታለን። ፍኖተ ነፃነት የተባለው የአንድነት ልሳን እራሱን የሚለካው በኮፒ ብዛቱ ከሆነ ባይሆን ሰዎቹ መሳሳታቸውን |የተቃዋሚዎች ሰፈር እንደምን ከረመ´ ብሎ በነካካው እጁ አባላቶቻችሁ ከልሳናችሁ ላይ የሚያገኙትን ግንዛቤ የተግባር መመሪያ ያደርጉ ዘንድ ይገባቸዋል ሲል ቢመክራቸው የተሻለ ይሆናል።

አልያማ ድርጅታዊ አቋም ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄው መንገዱን ስቷል ማለት ነው። በንድፈ ሀሳብ መጽሄት የድርጅት አባላቶች ንቃተ ህሊና ይዳብራል፣ ፖለቲካዊ ስብእና ይገነባል፣ ድርጅታዊ ቁርጠኝነትና አቋማቸው በማይናጋ መሰረት ላይ ይቆማል ፤የተግባር መመሪያ ሲያደርጉት ደግሞ አላማቸው ግብ ይመታል ማለት ነው። ሲጀመር ፕሮግራም የሌላቸው፣ ንድፈ  ሀሳባዊ ትንታኔ እንዲኖራቸው አይጠበቅም። ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ የሌላቸው ደግሞ በባህር አሸዋ ላይ እንደተገነባ ህንፃ ባስ ያለ ንፋስ የሚጥላቸው ይሆናሉ።

አቋማቸውም ደረጃ እየወጣ እንደሚገኝ ግለሰብ ወደኋላ ይሁን ወደፊት የማይታወቅ ነው። ስለሆነም ወጀብ በተነሳ ቁጥር ወዲህና ወዲያ ይወዛወዛሉ፣ ይፍረከረካሉ፣ ይሰባበራሉ፣ ይፈረካከሳሉ። የቅንጅት መሰባበር፣ ስንጣቂዎቹ አንድነቶች የተከፋፈሉት፣ የዜሮ ድምር አስተሳሰብ የአመት ቀለባቸውና የዕለት ጉርሳቸው የሆነው ከዚሁ የተግባር መመሪያ እጦት በመነጨ በሚደርስባቸው የአቋም መዋዠቅ ስለሆነም አይደል?። የአምሰተኛው ክፍል የመጣጥፍ ጥርቅሞችህን በአምስተኛው ክፍል ጨረፍታዬ እመጣበታለሁ።